# የጎንደር ሕብረት

Website: www.gonderhibret.org
Email: gonderhibret72@gmail.com

## ይድረስ ለጎንደር ሕዝብ ቁጥር #7

## ወያኔን ማመን፤ ውሃን እንድመጨበጥ ነው!

የጎንደር ሕብረት ዛሬም እንደ አለፉት መግለጫዎቻችን፤ በጎንደር ህዝብ ላይ የሚፈጽመውን የግፍ ተግባሮች አደባባይ በማውጣት፤ አገር አድን ብሔራዊ ትግላችንን የምናጠናክርበትን ስልት የማጠናከሩን ዓላማ ግብ ለማድረስ ነው። ይህ ሲባል ግን፤ በጦርነት ተወልዶ፤ በጦርነት እያረጀ ያለው፤ አገር አጥፊው የወያኔ ቡድን፤ በወረቀት ብቻ ይወድቃል ብለን ማመናችን አይደለም። መግለጫ፤ ጠላትን ያጋልጣል። ባንፃሩም ወገንን ያሥተባብራል፤ ያደራጃል፤ ያሥታጥቃል፤ በመጨረሻም ጠላቱን ይደመሥሳል።

ባለፉት 25 ዓመታት የጎንደር ሕዝብ የተፈጸመበትን ሰቆቃና ግፍ ለመዘርዘር በየጊዜው በምናወጣቸው ጥቂት ገጾች ላይ ብቻ ተዘርዝሮ የሚያበቃ ሳይሆን ሙሉ መጽሐፍ እንኳ አይበቃውም። ወያኔዎች ዛሬም እንደ ትናንቱ በሕዝባችን ላይ አረመኒያዊ ጭፍጫፋ ለማካሄድ ኃይላቸዉን አጠናክረዉ ወደ መተማና ቋራ የግዛት መረባቸውን ለመዘርጋት ልዩ ቅልብ ጦር አሰማርተዋል ። ይህ ቅልብ ሰራዊት በወያኔ ካድሬነት ለፖለቲካ ተግባር ተሰማርቶ የሁለቱን ማህበረሰብ ለማጋጨት ለቅማንት ወገኖቻችን ከናንተ ጋር ነን አይዟችሁ ሲሉ፤ ለአማራዉ ማህበረሰብ ደግሞ ከናንተ ጎን ሁነን ቅማንትን ድራሹን እናጠፋለን እንደሚሉ ከመሬት ላይ በነጋዴ ባህር፤ በዳንጉራ እና በዳዋ የተረጋገጠ መረጃ ደርሶናል። ይህ አገርን ለማጥፋት ትዉልድን በጥላቻ የመበከል በሽታን እያጋብን ያለን መሰሪ ኃይል፤ የዘር ጎራ ሳንለይ በህብረት ጠንክረን መዋጋት እና ራሳችንን ነፃ ማውጣት፤ ታሪካዊ እና አገራዎ ግዴታችን ነው።

ጎንደር ህብረት የሁሉም ህብረተሰብ አካል በመሆኑ የወያኔወችን የድብቅ መርዝ መርጨትና የጥፋት ዘመቻ በየቀኑ ከጉኛቸዉ ዉስጥ ገብቶ ሴራቸዉን ፈልፍሎ እያወጣ ነዉ። ሌላዉ የፌደራል ተብየዉ ወታደር ዋና ስራ የወያኔ ፖሊት ቢሮ የሚወስነዉን ማስፈጸም ብቻ ስለሆነ የሱዳንን ድንበር ለማካለል የጠረፉን ህዝብ ቀስበቀስ እያፈናቀሉ የትግራይ ነጻ አዉጭ ግንባርን ሚሊሻ ማስፈር ነዉ። ባለፈዉ ወር በበረከት ሰሞኦንና አባይ ፀሐዬ የተመራዉ ቡድን ልዩ ሰራዊት ለማስፈር በአስቸኳይ እስከ ጠረፍ ድረሥ የተጓዘው ለዚህ ዓላማ ነበር። በጠረፍ አካባቢ ያሰፈሯቸዉን የትግራይ ሚሊሻ ቤተሰቦች አደጋ እንዳይደርስባቸዉ ለመታደግ እንጂ፤ በፍጹም ለጎንደር ህዝብ ሰላም ተመኝተዉ እንዳልሆነ ህዝባችን እንዲያዉቀዉ እንፈልጋለን።

እሄን ሥንል በተጨባጭ መሬት ላይ የተፈጸመውን ዕውነት አብነት በማድረግ ነው። ቅማንትና አማራ ተጋጨ በሚል ድብቅ ሴራ የሰለጠኑ ወታደሮችንና ሚሊሻወችን በአማራና በቅማንት ኗሪዉ ህዝብ አሥርጎ በማሥገባት፤ ጦርነት ከለኮሱ በኋላ፤ ይፋ ጠርነት አዉጀዉ ጎንደርን ከሁለት ለመክፈል ባደረጉት ሙከራ ለማመን በሚያቅት መልኩ አብረው የበሉ እና ይጠጡ የነበሩ ወንድማማቾች፤ በጋብቻ ይኖሩ የነበሩ ቤተሰቦች ለማዳማት የጦርነት ዘመቻ ተካሂዷል፤ ንብረት ወድሟል፤ በሺወች የሚቆጠሩ ተፈናቅለዋል።

በአለፉት ሶስት ወራት ሰዉ በጥይት ሲቀሰፍ አንድም የወያኔ ባለስልጣን ብቅ ያለ አልነበረም። በሚከተሉት አካባቢወች ሥራ አጦችን በገንዘብ እየገዙ ክብር የሆነዉን የሰዉ ህይወት በማጥፋት ሥራ አሰማርተዉ ጉዳት አድርሰዋል።

በትክል ድንጋይ፤ በማዉራ፤ በሮቢት፤ በነጋዴ ባህር፤ በሸህዲ፤ በአይከል፤ በጭንጭቅ፤ በዳንጉራ፤ በዳዋ ፤በአዳኝ አገር፤ በአብደራፊ፤ በአብርሃ ጅራ፤ በቋራ፣ በመተማና ወልቃይት ጠገደ/ሁመራ ግፍ ሲፈጸም ወያኔወች ፌደራል ይዘዉ ብቅ አላሉም። አሁን ጀግናዉ የቋራ፤ የመተማ፤ የአርማጭሆ የሁመራ፤ የወልቃይት ጠገዴ ህዝብ በአንድነት ቁሞ ድንበራችን እናስከብራለን ሲል ቅማንትና አማራን ልናረጋጋ፣ እርቀ ሰላም ልንፈጥር በሚል የታጠቁ ሚሊሻ እና ጀሌወችን እያሰማሩ ነዉ። እውነቱ ግን አሁን ትንሽ እየተረጋጋ ያለውን ወገናችን ወደሌላ የከፋ ርስ በርስ ጦርነት ለመዘፈቅ የታቀደ ተንኮል ነው። የጎንደር ህዝብ ይህ ለጥፋት የተሰማራ ሰራዊት ወገኖቻችን የሚጨፈጭፍ እና የሚያጨፋጭፍ፤ በድብቅ የሚያፍን መሆኑን ተገንዝቦ ሁሉም ህዝብ በአንድነት ተሰልፎ ከአካባቢው ማስወጣት አለበት። ህዝብ በርቅ ያበረደዉ ሰላም ያስጨነቀዉ ወያኔ እንደገና ግጭት ለመቀስቀስ በሸህዲ ባለፈው ሳምንት 6 በዚህ በያዝነው ሳምንት ደግሞ 8 ቤተሰቦችን አፍኖ በድብቅ የግፍ ግድያ ፈጽሟል። አሁንም የሁለቱን ማህበረሰብ የመካለልን ዓላም የሚያስፈጽሙ ድብቅ ኮሚቴወችን በካድሬነት አሰማርቷል። የጎንደር ህዝብ እኒህን ዉሻወች በየመንደሩ ማስወጣት አለበት።

ለመሆኑ በጎንደር ላይ ደባ ሲሰራ፣ ተወላጅ የሆኑ ምሁራን፣ ሊቃዉንት፤ በመማርና በማስተማር ተቋም ያላችሁ፤ እንዲሁም ብአዴን ዉስጥ ለዕለት ጉርስ ለወያኔ ያደራችሁ ምን ነካችሁ? የቅማንት ማህበረሰም በዘር አንከፋፈልም ብሎ ለአብሮነት ያደረገዉ ትግል ቢያንስ ተደብቃችሁ ለምን ታሪኩን አትጽፉም። ገና ወያኔ እንደገባ ጎንደር ሲኒማ አዳራሽ ቅማንትን በጎሳ ጎራ ለይ ብሎ ስብሰባ ሲጠራ መላዉ የጎንደር ከተማ ህዝብ አማራዉም ቅማንቱም ሁላችን ቅማንት ነን ብሎ አስደንግጦ ቅስሙን መስበሩን አትመሰክሩም።

በእርግጥም እዉነቱ ከተነገረ የጎንደር ህዝብ ከጅምሩ እስከ አሁን የወያኔን ዘረኛነት በጥብቅ ተዋግቷል። ነገር ግን በድብቅ ስራዉን አጠናክሮ ቀጠለ። በየጣቢያዉ አስተዳደር የወያኔን ካድሬወችን ምክትል አድርጎ ሾመ። አሁን ከሃያ አምስት አመታት በኋላ በዘር የተደቃሉትን፤ በሃብት ሙስና ያኮላሻቸዉን አባዉራወች አሳምኖ፤ ብአዴንና ኦዴድ ስለ አንቀጽ 39 ከሰለጠኑበት ፖሊት ቢሮ መቀሌ አመላልሶ፤ ወያኔ ከገባ የተወለዱ ህጻናትን በዘር ፖለቲካ አጥምቆ፤ የቅማንትን ታሪካዊ ስም በመሰረዝ ለህዝብ ቆጠራ ቅጽ አዘጋጅቶ ለብአዴኖች አስረክቦ፤ ለክልል ካልታገልክ ከእንግዲህ ቅማንት የሚባል ስም የለም የሚለዉን ሴራ የሚያጋልጥ እንዴት አንድ ጎንደሬ የብአዴን አመራር/አባል ጠፋ?።

በጎንደር በተደጋጋሚ ጥናት ተደርጎ አብዛኛዉ በዘር መከፋፈልን ተቃዉሟል። ማንነቱን ለማግኘት ሲባል ባይሆን የተወሰኑ 42 ቀበሌወች ይከለሉ የሚለዉ የንቀት እና የግፍ ቀንበር ለምን ተጫነበት? በጉልበትእና በጦርነት የቅማንት ሙሉ ጎንደሬነት ለማሳጣት ለምን ተፈለገ? የቅማንት አርበኞች፤ የቅማንት ምሁራን በብቃት ጎንደርን

# የጎንደር ሕብረት

Website: www.gonderhibret.org

Email: gonderhibret72@gmail.com


ለዘመናት መርተዋል እኮ። ህዝቡ የመሰከረዉ እዉነታ ይህ ነዉ። አማራ ያልሆኑ ብአዴኖች የቅማንት የጎንደሬ ምንነት፤ የአብሮነት ታሪክ ሲያደበዝዙ ከነ አቶ በረከት በታች ያሉት ጎንደሬወች ለምን ወጥተዉ ሃቁን በመናገር ጎንደርን ለማዳከም የተሰራዉን የወያኔን ድብቅ ሴራ አይናገሩም። በይፋ መመስከርን ከፈሩ በሚስጢር ለምን ብዕራቸዉን በወያኔ ላይ አይቀስሩም። ስንት ጊዜ ሆድ አደር ሆኖ የሰዉ ፍጡር አጎብድዶ ይኖራል? ስንት ሺ ዓመትስ እንኖራለን?።

## <u>አሁንም በድጋሜ ይድረስ ለትግራይ ህዝብ</u>

የዛሬ መልዕክታችን ለትግራይ ህዝብና በክፍለ ሃገሩ ዉስጥ ለፍትህና ለእኩልነት ለሚታገሉ ዲሞክራሲያዊ ሃይሎች ነዉ። በትግራ ህዝብ ስም የሚነግደዉ ወያኔ በወልቃይት ጠገዴ፤ ጠለምት፤ እና ሁመራ ህዝብ ላይ የዘር ማጥፋት ወንጀል ፈጽሟል። ይህንን አካባቢ ወያኔ በጉልበት አስገድዶ ወደ ትግራይ ሲጨፈልቅ እና በሃይል የማካለል ፖሊሲ ሲተገበር ኑዋሪዉ ህዝብ ለዘመናት ከኖረበት ተፈናቅሎ፤ እስራት፤ ግድላት ተፈጽሞበታል። ጎንደሬ ነኝ በማለቱ የባርነት ኑሮ እንዲኖር ተገዶ ቆይቷል።

ለፍትህ፤ ለእኩልነትና ዲሞክራሲ የሚታገሉ ለህዝብ የቆሙ ታጋዮችም ሆነ የትግራይ ህዝብ ድርጊቱን በማዉገዝ የወልቃይት ጠገዴን ትግል መደገፍ ለወደፊት ጉርብትና እጅግ ወሳኝ ነዉ። የጎንደርና የትግራይ ታሪካዊ ወሰን ተከዜ ነዉ። በዚህ ጉዳይ ላይ ህዝብ ምላሽ ይሰጣል ብለን እናምናለን። ግልጽ አቋም ወስዶ ከጎንደር ህዝብ ጎን መቆሙንና የሁለቱ ክፍለ ሃገራት ህዝብ በፍቅር አብረዉ የሚኖሩበት አስተማማኝ ሁኔታ እንዲፈጠር የወልቃይት ጠገዴን የጎንደሬነት ጥያቄ አግባብ መሆኑን በጽሁፍም ሆነ በአንደበታቸዉ የትብብር መልዕክት እንዲያስተላልፉ በአክብሮት እንጠይቃለን።

በአጠቃላይም ለህዝቦች እኩልነት የሚታገሉ ድርጅቶች ሁሉ ወያኔ በወልቃት ጠገዴ፤ ሁመራ፤ በጎንደር ዳባት አዉራጃ ህዝብ ላይ የተፈጸመዉን ድርጊት እና ጎንደርን በዘር ከሁለት ለመክፈል የሚደረገዉን ሴራ በአደባባይ አዉግዘዉ ለወልቃይት ጠገዴ ህዝብ በጎንደር አስተዳደር እንደነበረዉ የመሆን የሙብት ትግል አጋርነታቸዉን እንዲገልጹ እናሳስባለን።

ተከዜን ተሻግሮ ትግሬ ናችሁ፤ በጉልበት እናስተዳድራችሁ በሚል እብሪት ወያኔ ያካሄደዉን አንድን ዘር አፈናቅሎ ሌላን ዘር የመተካት አፈና ሥራ መወገዝ አለበት። ይህ ሰቆቃና ግፍ ለዘመናት በጉርብትናም ሆነ በጎንደር መሬት አብሮ የኖረዉን ህዝባችን ሰላም እስከ ወዲያኛው የሚያደፈርስ በመሆኑ፤ የትግራይ ህዝብ ከጎናችን ሁኖ በምንወዳት ሃገረ ኢትዮጵያ በፍቅር ተሳሥሮ በአንድ ላይ ለመኖር የሚያስችለን ስርዓት ተባብረን ለመገንባት የዜግነት ግዴታ አለብን። የወልቃይት ጠገደዴ መሬት በጉልበት የተካለለ፣ መላዉ የጎንደር ህዝብ ሳይጠየቅ በመሳሪያ አፈሙዝ የተወሰደ በመሆኑ በአቸኳይ መፈታቱ እጅግ አስፈላጊ ነዉ የሚል የጸና እምነት አለን።።

በቅርቡ የጎንደር ህዝብ የወልቃይት ወገኖቻችን የአማራነትናና የጎንደሬነታቸዉን በጉልበት በመነጠቃቸው ምክንያት ድምጻቸዉን ከፍ አድርገዉ ሲናገሩ፤ አይደለም የጎንደር ሕዝብ፤ መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ከምንጊዜዉም በበለጠ

ጭሆታቸዉ እያዳመጠ ያለበት ወቅት ላይ ደርሰናል። ብሶታቸዉን በአደባባይ እንዲያሰሙ እና በሰላማዊ መንገድ እንዲፈታ ከጎናቸዉ ቁሟል። በክልሉ ተንቀሳቅሰዉ ጎንደሬኔታቸዉና እና በዘር ደረጃ ከመጣ አማራ መሆናቸዉን በአንደበታቸዉ ሲናገሩ የጎንደር ህዝ በአንድ ድምጽ አንጨብጭቦ ተቀብሏል። ከአሁን በፊት እንደጠቀስነዉ አስፈላጊ ያልሆነ ጦርነት እንዳይቀሰቀስ የወያኔ ሚሊሻ፤ ካድሬና ልዩ ታጣቂወች ከተከዜ ወዲህ ተሻግረዉ ማስገበሩን፤ በሴት እህቶቻችን ላይ ግፍ መፈጸማቸዉን አንዲያቆሙ በድጋሜ መልክታችን እናስተላልፉለን። ወያኔ ትግራይን እወክላለሁ በሚል በስሙ የመነገድ ሙስና እና ጎንደርንም መላዉ ኢትዮጵያን የመንከስ ልክፍት የማስቆም ሃላፊነት ከፍተኛዉን ድርሻ የትግራይ ህዝብ አለዉ ብለን እናምናለን።

ሌላዉ ሳናነሳ የማናልፈዉ አኩሪ ታሪክ፤ ደጉ እና ሰላም ወዳድ ወገኖቻችን፤ የቅማንት እና የአማራን ህዝብ እርስ በእር ለማዳማት የተለኮሰዉን እሳት ለማጥፋት፤ ለግል ህይወታቸው ሳይፈሩ እና ሳይሳሱ በጠመንጃ አፈሙዝ አልፈው መሃከል ጣልቃ እየገቡ የፈጸሙትን የማሥታረቅ ቅዱስ ተግባር ነዉ። የሚያሳዝነዉ ግን ለዚህ የተቀደሰ አላማ የተሰለፉ ሽማግሌወች ላይ በስዉር ግድያ ተፈጽሟል፤ ይህ ደስታችን በሃዘን ለዉጦታል። ከዚህ በመማር የጎንደርን ህዝብ አደራ የምንለዉ፤ የሰላም አባቶች ጉዳት እንዳይደርስባቸዉ በንቃት እንዲጠብቅ ነዉ። የወልቃይት ጠገዴ የሰላም እና የመብት ኮሚቴወችም በጎንደርና በትግራይ ህዝብ መራራቅ እንዳይኖር ያለጦርነት በሰላም እንዲፈታ ከልብ እየሰሩ እንደሆነ ህዝብ እምነት ጥሎባቸዋል። በነሱ ላይም ጥይት ቀርቶ ዝምብ እንዳያርፍባቸዉ። የወልቃይት ጠገዴ ህዝባዊ ኮሚቴ ከትግራ ሽማግሌወች ጋር ተማክሮ መፍትሄ ከህዝብ እንዲመጣ ተግቶ እንዲሰራ መልካም ምኞታችን ነዉ።

ወያኔ፤ ህዝባችን ሰላም ሲመኝ የእርስ በእርስ ግጭት የሚያቀጣጠለዉ አገር ዉስጥ ብቻ ሳይሆን፤ አገር ውሥጥ ህዝባችን በርሃብ እንደ ቅጠል እየረገፈ፤ በዉጭ አገር 50 ሚሊዮን ባጀት መድቦ፤ ዉጭ ያለዉን ኢትዮጵያዊያን ማሰለፍ ባይችሉም የሙስና ጥቅም ያሸነፋቸዉ፤ ለአገር ቅንጣት ያህል ደንታ የሌላቸዉ ጥቂት ሆዳም ቡችሎችን በመመልመል፤ ኮሚኒቲያዎቻችን እና ቤተ ክርስቲያኖቻችን ሲያበጣብጡ ይታያሉያሉ። እነዚህ ጥቂት የወያኔ ሎሌ ቡችሎች፤ በመዋለ ንዋይ የሰከሩ፤ በዘርና በጋብቻ የተሳሰሩ ግለሰቦችን በአማራና በቅማንት ስም ገንዝብ እየላኩ የሁለቱን ወገን ለማዳማት ሌት ከቀን የወያኔን ተልኮ የሚያስፈጽሙ እንዳሉ አረጋግጠናል። በተለይ በካናዳ፤ እና በምድረ አሜሪካ ውስጥ፤ በዋሺንግተን/ሲያትል፤ በፖርት ላንድ/ ኦሬጋን፤ በካሊፎርኒያ/ሎስ አንጀልስ፤ በዴንቨር /በኮሎራዶ፣ በአትላንታ/ ጆርጅያ፤ ገንዘብ እየላኩ ሕዝባችን ለማጨፋጨፍ ተግባር እንዲዉል የሚጎተጉቱ እንዳሉ የጎንደር ህዝብ እንዲያዉቀዉ እንፈልጋለን። አስፈላጊ ሁኖ ሲገኝ ሙሉ ስም ዝርዝራቸዉን ለህዝብ እናሳዉቃለን።

እኒሁ ሆዳም ካድሬዎች፤ ይህን አሥቀያሚ በደም የተነከረ እጃቸውን ያፀዱ መሥሏቸው ለሽፋን የሚጠቀሙት የወሬ ዘመቻ፤ “የጎንደር ሕብረት ብዙ ሰራዊት አስታጥቋል፣ ለአማራዉ ክልል 2 ሚሊዮን ልኳል”፤ የሚሉት የአሉባልታ ወሬ ከአባታቸዉ ከወያኔ የተቀኙት ተንኮል እና ወገኖቻችን ለመከፋፈል የሚጠቀሙት የሃሰት ዘመቻ መሆኑን እናረጋግጣለን። ወያኔዎች፤ ችግሩን ያመጡት እነሱ፤ የእርስ በእርስ ጦርነት የፈጠሩት ግድያዉን የመሩት እነሱ ሆነው እያለ፤ አሁን ህዝብ በእርቅ ያስቆመዉን ጠልፈዉ “እያስታረቅን ነዉ” እያሉ በጎን ቅማንትና አማራ

የሚካለልበትን ተግባር ላይ ለማዋል እና ህ/ስቡን ለማሳመን በራሪ ጽሁፍ በማሰራጨት ላይ ናቸዉ። ወያኔ ዶክመንተሪዉን የሰራዉ ህዝቡን በቅራኒ ዉስጥ ለማስገባት የታለመ እና የጎንደር ህብረት የሁለቱ ህዝቦች ዉሃና ወተት ናቸዉ የሚለዉን ጽኑ ዓላማ በጥላቻ ለመቀባት የተሞከረ ነዉ። የጎንደር ህዝብ ጎሕን የእዉነተኛ ልጆቹ ድርጅት እንደሆነ አዉቋል።

ጎንደር ህብረት የሚታገለው፤ ህዝባችን እንደ ቀደምቱ በአንድነት እና በፍቅር ተሳስሮ እንዲኖር ብቻ ነዉ። በአሁኑ ወቅት የተጣላ ታርቆ በአንድነት በመቆም ጎንደርን ያድን ነዉ። አንድ ጎንደሬ የወንድሙን ነብስ ካጠፋ እርጉም ጥቁር ዉሻ ዉለድ ተብሏል። ይህ የጎንደር ህዝብ ድምጽ ነዉ። ለዚህም ነዉ፤ ዘረኝነትና ጭቆና፤ የአጥፍቶ ጠፊዎች ዘረፋ ያንገፈገፈዉ ነፃነት የጠማዉ ኢትዮጵያዉዊ ሁሉ ለጎንደር ሕብረት ድጋፉን እዬሰጠን ያለው።

ይህ ሕዝባዊ ድጋፍ ያሥደነገጣቸው የቅማንት ተወላጅ እና ተቆርቋሪ ነን የሚሉ የወያኔ ካድሬዎች፤ አባታቸው ባሰለጠናቸው፤ እና በአንድ ወቅት የኢቲቢ (ETV) ቀን ከሌት ህዝብ ቲቪን ማየት እስኪጠላ “ጀሃዳዊ ሀረካት” በሚል የሞኝ ጨዋታ ሲያደናቁር እንደነበረው አይነት፤ የጎንደር ህብረት ተወካዩችን ቃለመጠየቅ በቁንጽሉ ቀጣጥለዉ ቅማንታዊ ሀረካት ቪድዮ በማቅረብ ህብረተሰባችንን እርስ በእርስ ለማፋጀት አቅደው ተነሥተዋል። ሆኖም፤ የጎንደርም ሆነ አጠቃላይ የኢትዮጵያ ሕዝብ የዚህ አይነቱ ሃረካት ሰልችቶታል፤ ከነቃም ቆይቷል። በወልቃይት ጠገዴ ህዝብ ላይም አዲስ ግን ዉዳቂ የሆነ ድራማ ይዘዉ ብቅ ብለዋል። ጎንደሬም አይደለ ትግሬም አይደለ ስለዚህ የራስ ገዝ አስተዳደር መጠየዬቅ ይገባዋል ይላሉ፤ ደሮን ሲደልላት በመጫኛ ጣሏት ይሉና የዘር ማጥፋት /ማጽዳት ተፈጽሞበት ባዶ የቀረዉን በቅኝ ግዛት የተያዘ የጎንደርን መሬት ሪፈረንደም የራስ አገዝ ብሎ ቀልድ ለጎንደር ህዝብ አይሰራም ከተከዜ ምላሽ ያለዉ ታሪካዊ ትግል ይቀጥላል። የወልቃይት ጠገዴን ህዝብ ያስጨረሱ የነ አዜብ ጎላ የቁም ሙቶች በኢትዮሜዲያ የለጠፉት ዲስኩር ከንቱ ነዉ።

ሆኖም በምንም ይሁን በምን፤ እውነትን መሸፈን አይቻልም ትግሉ በመላ ኢትዮጵያችን ተቀጣጥሎ አንድ እርከን ከፍ ብሏል። በመሆኑም “የነብር ጅራት አይዙም፤ ከያዙም አይለቁም” እንዲሉ ወያኔ አሁን ማምለጫ በሌለዉ የህዝብ አንድነት ትግል ገመድ ተጠልፏል። ጉሮሮውን ሲያዝ ሰላም በሚል ሊያዘናጋ ይሞክራል። ሆኖም ወያኔ ሰለአምን ሽቶ አያውቅም። መግደል እንጂ እስከአሁን ሞትን አያዉቅም። አሁን ግን የሞት ጽዋዉ የርሱ ነዉ፤ ለዚህ እርግጠኞች ነን። የጎንደር ህዝብ ከእንግዲ ትጥቁን አይፈታም። ኢትዮጵያዊ ወገናችንም ሆነ የጎንደር ህዝብ የወልቃይትን የጎንደሬነት፤ ታሪካዊ ምንነት ትግል እንደአይኑ ብሌን አይቶ ጥሪዉን ተቀብሎ በአጀንዳ ይዞታል። ይህ ለወያኔወች በእርግጥ መርዶ ነዉ።

ሌላው፤ ባለፈው መግለጫችን ለማስገንዘብ እንደሞከርነው፤ አሁንም በኃይለ ቃል እንደግመዋለን! ያለምንም ጥርጥር በሱዳን ባለሥልጣናት አንደበት እየተመሰከረ ባለው፤ በጠቅላይ ሚኒስተር ኃይለማሪያም ደሳለኝ እየተደገፈ ያለው እውነት፤ ወሰናችን አስከብረው በርሻ የተሰማሩ ወገኖቻችን ደንበር አልፈው የሱዳንን መሬት እያረሱ እንዳሉ፤ እነሱም “ሽፍታዎች” እደሆኑ እና ከዚህ ዓመት በኋላ ለሱዳን አስረክበው እንደሚወጡ ስምምነት ላይ

እንደደረሱ ተረጋግጧል። ታዲያ ምነው ወገን!! በጀግኖች አባቶቻችን ደም ታፍራና ተከብራ የኖረችው አገራችን፤ እንዴት በኛ ጊዜ፤ አገር እና ታሪክ እንደ ዳቦ ቅርጫ ሲቸበቸብ፤ እያየን ወኒያችን ተሰለበ። ነገ ለልጆቻችን የምናሥረክበው አገር እና ታሪክ፤ "የኛ ነበር፤ ወኢያኔ ለሱዳን ፈርሞ ሲሰጥ፤ ፈርተን ዝም አልን"!! ልንል? ትናንት ወደብ አልባ፤ ዛሬ ደግሞ አገር አላቦ!!

የጎንደር፤ የጎጃም፤ የወለጋ፤ ሕዝብ ሆይ! ዛሬ የርሻ መሬትህ ለአንዴ እና ለመጨረሻ ለባዕድ ተላልፎ እየተሰጠ፤ አንገትክን ደፍተህ በማዬት ጊዜ የምትሰጥ ከሆነ፤ መሬትክን የነጠቁህ ነገ ደግሞ ሚስትህን እንደሚጋሩህ አትጠራተር። አንተ ለራስህ ሳትታገል፤ መላው የኢትዮጵያ ህዝብ ሊደርስልህ አይችልም። የድሮውን እንተወው እና፤ ትናንት ሁሉም ኢትዮጵያዊ፤ ባድሜ ላይ ሄዶ "ደንበር ተደፈረ" ብሎ ደሙን ያፈሰሰው፤ አጥንቱን የከሰከሰው፤ የጦርነት ቃታውን ቀድመው የሳቡ፤ የመስዋዕትነቱን አቦል የቀመሱትን በአካባቢው የሚኖሩት የትግራይ ወገኖቻችን ደም ስለጮኽ ነው። የኦሮሞ ወገኖቻችን፤ በማሥተር ፕላን ስም ወያኔ በግፍ ገበሬውን እያፈናቀለ የሚቸበችበውን መሬት ያሥቆሙት፤ ከመቶ አርባ በላይ ህይወት ገብረው በአይበገሬነት ባደረጉት ቆራጥ ትግል ነው።

አዎ! በሥጋ ሞትን የምናሸልበው አንዴ ብቻ ቢሆንም፤ ከሞት በኋላ፤ ጥለን የምናልፈው ታሪክ ደግሞ ለጀግኖች፤ ህያው ታሪክን፤ ለሆዳሞች እና ለአገር ሻጮች ደግሞ፤ ሁለተኛ ሞትን ጥሎ ያልፋል። ዛሬ ላይ ቆመን የምናወድሳቸው፤ እነ አፄ ቴዎድሮስ፤ እነ አብዲሳጋ፤ እነ በላይ ዘለቀ፤ እነ ዘራዓይ ደረስ፤ እና የመሳሰሉት ጀግኖቻችን፤ በሥጋ ቢያሸልቡም ለአገር እና ለወገን በከፈሉ የህይወት ዋጋ፤ ለዘለዓለም ህያው ሆነው ስለኖሩ ነው። እኛስ ምርጫችን ህያውነት፤ ወይስ የሞት ሞትን በፍርሃት መውረስ? እናም የጎንደር ሕብረት፤ በአገር መሪነት ሥም በተቀመጡ አገር በቀል ጠላቶቿ ደላላነት ለሱዳን እየተቸበቸበች ያለችዋን አገራችን፤ መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ፤ ሆ! ብሎ በመነሳት ይታደጋት እንላለን። በአንጻሩም ወያኔወች ትናንት አገራችን በድብቅ ተደራድራችሁ፤ ዛሬ አይናችሁን አፍጥታችሁ ሽጣችኋል እያልን ነዉ። ኢትዮጵያንና ህዝቧን አታዉቁም፤ ስልጣን መልቀቁ ለናንተም መልካም ነዉ እንላለን።

## <u>የህበረት አስፈላጊነትል፦</u>

በእርግጥም በአሁኑ ወቅት ፍጹ የሆነ ህብረት መፈጠሩን የጎንደር ህብረት በጽኑ ያምናል። ጎንደር አንዷ የኢትዮጵያ ክፍለ ሃገር እንደመሆኗ ሁሉ፤ ከሌሎች ጋራ ተባብረን ካልታገልን ጎንደርን ብቻ ከወያኔ መከራና ሰቆቃ ነፃ ማድረግ እንደማይችል መገመት ፈላስፋ መሆንን አይጠይቅም። ነገር ግን ብዙ አገር ለመሆን እያሰብን በተናጠል ታግለን ኢትዮጵያንም ሆነ ህዝቧን ነጻ ማዉጣት አንችልም። ወያኔ በጎሳ ከፋፍሎ ሲያጋጨን፤ አይናችን ጨፍኖ አማራና ኦሮሞ ጠላት ናችሁ እያለ 25 ዓመታት በባርነት ሲገዛን፤ እኛ በወያኔ ዘረኛነት ተሳክረን እንዴትስ ህዝባችን ነጻ እናወጣለን? እንደ ጎንደር ህብረት እምነት በቅድሚያ አገራችን ኢትዮጵያ የምታገናኘን የአንድነታችን ምሰሶ መሆኗን እንተማመን። አሁን የምንፈጥረዉ ህብረት በዚች አገር የህግ የበላይነት፤ ፍትህ እና እኩልነት ሰፍኖ ያለምንም ተጽኖ ህዝቡ መሪዉን እንዲመርጥ ተስማምቶ አንድ ወጥ በሆነ ትግል ወያኔን ለመጣል እናብር።

ለዚያም ህዝቡ የወደፊት እጣዉን መክሮ እንዲወስን ዲሞክራሲያዊ መድረክ ማመቻቸት የመላዉ ድርጅቶች ህብረት አላማ መሆን አለበት፤ ከዚህ የተሻለ አማራጭ ካለ በጠረጴዛ ዙሪያ መመካከር። ከወያኔ ዉድቀት በኃላ ህብረቱ በጋራ ህዝቡ የሚለዉን ማዳመጥ ከህዝብ የተገኘዉን መልክት መሰረት ያደረገ ፖሎሲ ማርቀቅ። ህዝቡ በዘር፤ በቋንቋ ፌደራል እንፈልጋለን ካለ የህዝብን ዉሳኔ መቀበል፤ ወይም በመልክዓ ምድር፤ በኢኮኖሚ በባህል ትስስርን መሰረት ያደረገ ካለ ያን የህዝብ ዉሳኔ ለመቀበል ከአሁኑ ለህዝብ ቃል መግባት የህብረት መሰረታዊ ቁም ነገሮች መሆን አለባቸዉ። የጎንደር ሕብረት ምኞት ከዘር ከሃይማነት ጋር ያልተገናኘ የአስተዳደር ሥርዓት እንዲመሰረት ነዉ። ማለትም የመልክዓ ምድር አቀማመጥን፤ ማህበራዊ ትስስን፤ የምጣኔ ሃብትን መሰረት ያደረገ፤ ከቀበሌ እስከ ፕሬዝዳንታዊ የቀጥታ ምርጫ ሂደትን የተከተለ እንዲሆን የጎንደር ሕብረት እንቅስቃሴ አስተዋጽኦ ለማድረግ ይታገላል።

## <u>ለኢትዮጵያ ህዝብ</u>

የጎንደር ህዝብ ከወያኔ ጋር በዘርፈ ብዙ ትግል ላይነዉ፤ ከጀርባ ከሱዳን ጋር ሁኖ ወገኖቻችን እያረደ፤ በዉስጥ መሬታችን እዬነጠቀ፤ ወላድ እናቶችን የማምከን መርፌ መዉጋት ወይም መድሃኒት ማምከን፤ የተበከሉ ምግቦችን ማስገባት፤ የመጠጥ ዉሃን መበከል፤ የትምህርት ስርዓቱ መግደል፤ የተመረቱ ምርቶችን ወደዉጭ እየሸጡ ያልተፈተሸ ምግብ ከዉጭ ማስገባት፤ እርስ በርስ በማጋጨት ምርትን በዕሳት እያጋዩ፤ ህዝብን ለርሃብ ማጋለጥ፤ በማዳበሪያ እዳ ህዝብን ቀፍድዲ በመያዝ፤ አርሶ የመብላት ተሰፋውን ማጨለም፤ የአማራን ዘር አፈናቅሎ የሌላን ዘር ማስፈር፤ ይህ ሁሉ በ21 ክፍለዘመን በሌላ አገር ያልተከሰተ ነዉ። በአገራችን እየተፈጸመ ያለዉ ጭፍጨፋና ግድያ በጎንደር ብቻ አይደለም ፤ መሬት ዘረፋን በሰላማዊ መንገድ የተቃወሙ ወንድም እና እህቶቻችን ደም በአምቦ ፤ በወለጋ፤ በአሪሲ፤ በሃረር ፤ በጎምጎፋ እየፈሰሰ ነዉ፤ ጩኸታቸዉን እያሰሙ ለፋሽሽት አንገዛም ብለዉ ከወያኔ ቅልብ ወታደር ጋር እየተናነቁ ነዉ። የኢትዮጵያ ህዝብ በጎንደርና በሁሉም ኢትዮጵ ህዝብ ላይ የሚካሄደዉን ጭፍጨፋ ተቃዉመን በአንድ ላይ በመነሳት ወያኔን ለአዴን እና ለመጨረሻ ጊዜ ማስወገድ አለብን።

የኢትዮጵያዉያን ደም በከንቱ እየፈሰሰ ወያኔወች ፍጹም አሸናፊ ሊሆኑ አይችልም። ኢትዮጵያውያን በግፍ የሚፈሰውን የወገኖቻችን ባየን ቁጥር፤ የአልበገሬነት ባህሪያችን በዕልህ እየተሞላ፤ ጀግንነታችን እያየለ ጠላቶቻችንን ግባ ከመሬት መጨመሩ ታሪካዊ እውነታችን ነው። በዚህ ሃቅ መሰረት፤ ሰፊዉ ህዝብ ያቸንፋልና፤ ተባብረን ወያኔ ከልስልጣን ማዉረድ አይቀሬ እዉነታ ነዉ። ከእንግዲህ ፋሽሽት አይገዛንም።

ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!

የጎንደር ሕብረት

የጎንደር ሕብረት

Website: www.gonderhibret.org

Email: gonderhibret72@gmail.com

---

**መወሰድ የሚገባዉ ሕዝባዊ እርምጃች፡-**

የወያኔ ንብረት በሆኑ የአገልግሎት ሰጭ ድርጅቶች ላይ እቀባ ማድረግ፤

ሰልፍ ሲጠራ ሁሉም ከገጠር እስከ ከተማ ሆ!! ብሎ መዉጣት፤

የመገናኛ መንገዶችን በድንጋይ ናዳ መዝጋት እና የወያኔን የመኪና እንቅሥቃሴ መገደብ!

የወያኔ ካድሬና ሰላዩችን ከአካባቢ ማባረር፤ ከህዝብ ወገን ያልሆኑትን በህብረት ማግለል፤

የነጻነት ታጋይ ሲታሰር ህዝብ ሆ!! ብሎ ወቶ ማስፈታት፤ ግብር አድሞ አለመክፈል፤

በመላ አገሪቱ የስራ ማቆም አድማ መምታት፣ትጥቅን በፍጹም አለመፍታት፤